# የፖለቲካ ስምንተኛው ሺህ

በልጅግ አሊ

-፩-

**እንዳይነጋ እንዳይመሽ ብልሃት ተገኝቶ**
**ጊዜውን መከላከል እንዳይቻል ከቶ**
**እንዲሁም በአለም ላይ አለ ብዙ ነገር**
**በዚያም ቢሉት በዚህ መሆኑ የማይቀር"።**

**ከበደ ሚካኤል**
**1957**

እነሆ የሚሆን እንደሚሆን፤ መሆን ያለበትም እየሆነ እንደሆነ ፣ የማይሆንም እንደማይሆን በከበደ ሚካኤል ተጽፏል ።

የወያኔ መውደቂያ ዘመኑ ቀርቧልና ይህን ጽሁፍ የሚያነቡ፣ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚረዱ ሁሉ የወያኔን መውደቂያ ያፋጥኑት ዘንድ ተነግሯል ።በዚህ ጊዜ ሃሳዊ መስሂ ፖለቲከኞችና ሠራዊቶቻቸው በሐሰት የሚምሉ በየዕለቱ ቃላቸውን የሚለዋውጡ መሪዎች ይፈጠራሉ። ጧት የተነናገሩት ለማታ አይደገምም ።

**በዚህ ጊዜ ተጠንቀቁ ።**

በዚህ ጊዜ አድርባይ ፖለቲከኞች የበግ ለምድ ለብሰው አሕዛብን የሚያስቱ፣ በሥልጣን ጥም አዕምሮአቸው ፣ልቦናቸው የተሠወረ ይመጣሉ። ነጣቂ ተኩላም ናቸው ። በዘመኑ ትውልድ ላይ በማር የተለወሰ መርዝ ይነዙበታል። እውነተኛ መምህር ለመምሰል በየአደባባዩ ስለ ሰላማዊ ትግል ይሰብካሉ ። በውስጣቸው ግን በግል የሚያገኙትን ጥቅም ያልማሉ ። እናንተ ግን አትመኗቸው ። እንቢ በሏቸው ።

**ሃገራችሁ በየቀኑ አደጋ ላይ ስለሆነች በዚህ ጊዜ ተጠንቀቁ ።**

እነሆ በፖለቲካው ምድር ወያኔ ምርጫ 2002 ዓ.ም በኋላ ፀጥታ ይሰፍናል፣ በምርጫው አካባቢ ታዋቂ የነበሩ ፖለቲከኞች ከምርጫው በኋላ ከአሕዛብ በሃፍረት ይደበቃሉ ፣ የወያኔ ጭቆና እየተባባሰ ይሄዳል ተብሎ የተነገረው ትንቢት እየተፈፀመ ነው ።እነዚህ ፖለቲከኞች ወያኔ ምርጫውን አሸንፌለሁ ብሎ ካወጀ በኋላ የረባም ተቃውሞ ሳያሰሙ ፣መሬት ከበደኝ ሳይሉ፣በተደበቁበት ጉድጓድ በሕዝቡ ላይ እያሾፉ ፣ እስከሚቀጥለው ምርጫ ይቀጥሉ ዘንድ ቀደም ብሎ ተነግሯል ። ንግርቱም እየተፈፀመ ነው።

እነሆ ለእነዚህ ሐሳዊ መሢህ ፖለቲከኞች በትንቢቱ መሠረት በምርጫው ላይ ያደረጉት ገድል እየታየ በወያኔ የጥቅም መዋቅር የተመደበላቸውን ፍሬ በሰላም ያጣጥሙ ዘንድ ጊዜው ደርሰል ። የሀሳውያን "የሰላም ትግል" ውጤት፣ የላባቸውም ፍሬ አብቧል። በደስታና በፍሰሐ ይቋደሱት ዘንድ ከፈጣሪያቸው ከወያኔ ተፈቅዶላቸዋል ።

**እነሆ ለእውነት የቆመ ሊታሠር ሊገደል ፣ለሆዱ ያደረ ደግሞ በሰላም ይኖር ዘንድ በወያኔ ሕግ ተደንግጓልና ቃሉም እየተፈፀመ ይገኛል ።**

እነሆ ብርቱካንም ከምርጫው በኋላ ትፈታለች የተባለው ቃል ደርሶ ፍፃሜ አግኝቷል። የአንድነት ድርጅት አባላት ዓይኖች በሙሉ ወደ እሷ ያፈጣሉ ። የተከፋፈሉት የድርጅቱ መሪዎች የኛ ደጋፊ ነች ለማለት ጥረታቸውን ይቀጥላሉ ተብሎ የተጻፈው እየተፈጸመ ነው።ድርጅቱን የከፋፈሉት መሪዎቹ ለብርቱካን ቦታውን ለቀው በአንድነት አይሰሩም ተብሎ የተነገረው ትንቢት ገሃድ ሆኗል ።በዚህ ዘመን የሚያሳዝን ተግባር ይፈፀማል።

ብርቱካን ከፖለቲካው ለመውጣት ከወሰነች ወይም ውጭ ሃገር ለመቅረት ካሰበች ታላቅ ደስታና ፍስሐ በተፋላሚዎቹ ክፍሎች ይሰፍናል ተብሎ የተፃፈው እነሆ እየደረሰ ነው። ተፋላሚዎቹ የወያኔን ድጋፍ የሚፈልጉ ስለሆኑ ለወያኔ ለማደር የሚደረገው ሽኩቻ በሰፊው እንደሚቀጥል ተጽፏልና አይቀርም ።

ለሕዝብ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ "ስለ ሰላማዊ ትግል" በሰፊው ይሰበካል። በአቋማቸው ጠንካራ የሆኑ ድርጅቶች ይሰደባሉ ፣ የመሣሪያ ትግል ይወገዛል ፣ ተብሎ የተነገረውን ይፈፀም ዘንድ ሰሞኑን በፓልቶክ ላይ ተጀምሯል ።በዚህ ጊዜ አድርባይ እንደ አሸን ይፈላል ።

**በዚህ ወቅት ለሃገር አንድነት የምታስቡ ግን ነቅታችሁ ጠብቁ ።**

የብርቱካንን መፈታት ምክንያት በማድረግ ከምርጫ 2002 በኋላ የተደበቁ በሙሉ ነፍስ ይዘራሉ ።መድረክ ይጠናከር ዘንድ ይሰበካል። አድር ባዮች ከምርጫው በኋላ የተጎናፀፉት የፍሰሐና የደስታ ጊዜቸውን ለማራዘም ይነሳሉ ። ከሰሜን አሜሪካ በተከታታይ የአድርባይነትን መንገድን የሚያሳዩ " እንግዲህ ወዴት" የሚሉ ተስፋ አስቆራጭ ቀመሮች ይጻፉ ዘንድ ተነግሯልና እየተፈፀመ ነው። ምሁራን ነን የሚሉ አዲስ የአድርባይነት ንድፈ ሃሳብ (ቲወሪ) እንደተለመደው ይዘው ይነሳሉ።በዚህ ወቅት ለሚቀጥለው ምርጫ አዲስ ፀሎት ይጀመራል ።

**"እነሆ ጌታችን ፈጣሪያችን ወያኔ ሆይ ፣ ለሰላማዊ ትግል የቆምን ነንና ምህረትህ አይለየን ። ዳግም ስላንተ መጥፎነት ለአሕዛብ ላናነሳ ፣ አምርርው የሚታገሉህን ልንዋጋ ቃል እንገባለን ። ምህረትህና ፀጋህ ከኛ ጋር ይሁን ። በመሳሪያ ሊፋለሙህ የተዘጋጁት እንዳንተው ሆነን ልንዋጋልህ ፣ ልናዋርድልህ ፣ ልናጣጥልልህ ፣ወኔያቸውን ልንሰልብልህ ቆርጠን ስለተነሳን በረከትን ስጠን ።"**

በዚህ ወቅት የሚቀጥለው ምርጫ ይደርሳልና አዲስ የመደራደሪያ የምርጫ ሕግ ለማውጣት ወያኔ ይራወጣል ። በዚህ ወቅትም አዲስ የወያኔ አዋጅ ይነገራል ።

**"እውነት እውነት እላችኋለሁ ከዚህ በፊትም እንደታየው ከምርጫ በኋላ የሚያተርፈው ከዛም ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በተድላና ፍስሐ የሚኖረው ዛሬ እኔ የምለውን የሰማና ከእኔ ጋር የተፈራረመ ነው ።እንኳን እሱ የልጁም ልጅ ያልፍለት ዘንድ ከዚህ በፊት እንደ አደረግሁት አሁንም አደርጋለሁ ። የታወቁ በሃገሪቷ የሚሰሩ ኮንትራቶችን እስጣለሁ ። ምን አልባት ኮንትራቶቹን በስማችሁ መቀበል የምትፈሩ ካላችሁ በልጅ ፣ በልጅ ልጅ ፣ በሚስት ወይም በውክልና አደረገው ዘንድ ከዚህ በፊት የተመሰከረ ነውና ጥርጣሬ ሊገባችሁ አይገባም ይህንን ጊዜ በሰላም የሚልፈው ከእኔ ጋር የቆመ ብቻ ነው ። አሕዛብ ምንም አያደርጋችሁም፣ የማድናችሁም ፣የማጠፋችሁም እኔው ፈጣሪያችሁ ወያኔ ነኝ ። ቃሌን የሰማና የተቀበለ ይበለጽግ ዘንድ ታይቷልና ።"**

እነሆ ወደሚቀጥለው ምርጫው ጉዞ በሰፊው ይጀመራል ። ጽሁፎች ድረ ገጾችን ይሞሉታል ።አዳዲስ አድርባዩች ብቅ እንደሚሉ ተነግሯልና በአዲስ ቲዎሪ ታጅበው ብቅ ይላሉ ። አሕዛብን ለማሰባሰብ ይጥራሉ ። አዲስ አዋጅ ይነገራል ። በዚህ ዘመን አድርባዮች ከሀብታቸው ከብልጽግናቸው የተነሳ የኢትዮጵያን አንድነት የሕዝቡን ሰቆቃ ይዘነጋሉ ።ከወያኔ የሚሰጣቸውን ጥቅማ ጥቅም የሚያከማቹበት ከፍተኛ ሣጥን ለማዘጋጀት ይፈጥናሉ ።

እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ ፣አንድነታችሁን አጠንክሩ ፣ በመካከላችሁ መለያየት አይኑር .እርስ በርሱ የሚለያይ ሕብረት ፈጥኖ ይጠፋል እርስ በርሱም የሚለያይ ውህደት አይፀናም ፈጥኖ ይወድቃል የሚለው ቃል ተክዶ አዲስ የአድርባይነት መፈክር ይጎላል ።በዚህ ጊዜ ብዙ የተቃዋሚ ፖለቲከኞች ወያኔን ለማስደሰት ፣ታማኝነታቸውን ለወያኔ ለማሳየት እርስ በራሳቸው ይጎነታተላሉ ። ከሥልጣን ጉጉት የተነሳ በተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችና በጭፍሮቻቸው መካከል ፍቅር ትጠፋለች ። መተማመን አይኖርም ። አንዱን ሌላውን እንደ አውሬ ይመለከተዋል ።

በአድርባይ ፖለቲከኞች አዲስ መዝሙር ይጀመራል ።

"እነሆ በሰሜን በኩል ነፃ እናወጣችኋለን ብለው የሄዱትን አትመኑዋቸው ፣ በትግል ውስጥ በጽናት ለብዙ ዘመናት የቆየውን ፓርቲንም አትመኑ ።ዘመኑ የኛ ነውና ለዘመናዊ ፖለቲካ ተዘጋጁ ።እነሆ ወያኔም ቃል ገብቷል ፣ እኛም ለውጥ እያየን ነው ፣ የሚቀጥለው ምርጫ ዲሞክራሲያዊ ሊሆን ነውና አሕዛብ ይሳተፍ "ተብሎ ይሰበካል ።

የወያኔ መሪዎችም አዲስ አዋጅ ያስነግራሉ . . .

" ማነህ ባለተራ ፣የወያኔ ወዳጅ ፣በሚቀጥለው ምርጫ ሥልጣን ለማስጠበቅ ያስጠመደ ፣ ሕገ መንግሥቱን የተቀበለ ፣ ከእኔ ጋር የሚተባበር ። ከአሕዘብ ተለይቶ ይቁም ። እኔ እስማው ዘንድ ድምጹን ከፍ ያድርግ ።"

በዚህ ዘመን በሆዳም ፖለቲከኞች ብዙ የአድርባይነት.ገድሎች ይነገራሉ ።

## ገድለ ልደቱ ( ከደቱ )

እነሆ ብላቴናው ምንም ገንዘብ የለውም ነበር ። የጫትና የሲጃራ መግዣ አጥቶ ፣ችግር አቆራምዶት በአውራ መንገድ ላይ ድዱን አስጥቶ ይውል ነበር ። መንገድ ላይ ተቀምጦ እያለ የወያኔ መልዕክተኛ በግልጽ ታየው ።እንዲህም አለው ።

"እነሆ አሁን ተነስ ።ሃዘንህና መከራህን ፈጣሪህ ወያኔ ተመልክቶልሃል ። ሂድና የፖለቲካ ተቃዋሚ ሁን ። ድምፅህንም ከፍ አድርገህ ስደበኝ ። በአሕዘብም ፊት አዋርደኝ ። በዚህም ምክንያት ደጋፊዎች ታገኛለህ ። እኔም ስምህ እንዲገን አስርሃለሁ ። አሕዛብ "ማንዴላ" ይሉህ ዘንድ ተጽፏልና ይፈጸማል ።በተቃዋሚነትህ ትታወቃለህ ። በተቃዋሚዎች ውስጥ ያሉ ደጋፊዎቻችን አንተን ከፍ አድርገው ሰለ አንድነት የሚጮሁትን ታዋርዳቸው ዘንድ መንገዱ ይከፈትልሃል ። ስለ አንድነት ጠንክረው የሚዋጉትን ታዋርዳቸው ዘንድ ተፅፋልና አንተም ታዋርዳቸዋለህ። የፖለቲካ ድርጅትም እንድታቋቁም እረዳሃለሁ ። ብዙዎች ከአንተ ጋር ሕብረትና ባስቸኳይም ውህደትን ይሰብከሉ ።ታላቅም ሰው ትሆናለህ። ይህንን ውለታዬን ቀኑ ሲደርስ አስታውስሃለሁ ። ከመንገድ ዳር መደበር ያነሳሁህ ነኝና አንድ ቀን ውለታዬን ትመልስ ዘንድ እጠይቅሃለሁ ። በዚህ የማትስማማ ከሆነ አሁኑኑ ቃልህን ልስማ " ።

ብላቴናውን እንዲህ ብሎ መለስ

"ጌታዬ ፈጣሪዬ ወያኔ ሆይ ! ክብርህና ዓላማህ ለዘላለም ይሁን ። ከዚህ የድብርት ኑሮ ፣ በአውራ መንገድ ላይ ድድ ማስጣት አንስተህ አዲስ የድሎት ኑሮ ያዘጋጀህልኝ እንዴት ብዬስ እክዳለሁ? ቀኑ ደርሶ ውለታህ መላሽ ያደርገኝ ዘንድ የዘወትር ፀሎቴ ነው ። አሕዛብ ውስጥ ባለሁበት ወቅት ከጎኔ ትቆም ዘንድ ፣ምክርህንም ታካፍለኝ ዘንድ እግርህ ላይ ወድቄ እለምንሃለሁ ። ተሳስቼ ብዙ እንዳላጠፋ ታስጠነቅቀኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ። ክብር ምስጋና ለአንተና ለመንግስትህ ይሁን ።"

ወያኔም "ተባረክ ልጄ ። እንግዲህ ተነስና ጉዞህን ጀምር ።" ብሎ አዘዘው ።

ልደቱም ታዋቂ ፖለቲከኛ ሆነ ። ወያኔም ለማስመሰል አሰረው ። በእስር ቤት ውስጥ ይንከባከበው ጀመር ። ስሙም ገነነ ። "ማንዴላም " ተብሎ በአሕዛብ ተሰየመ ።የቆዩ ፖለቲከኞች መንገዱን ለእሱ ይለቁ ዘንድ ተነገራቸው። ብላቴናው ከወደቀበት ተነስቶ የአውሮፓን ፣ የአሜሪካንን ከተሞች ይጎበኝ ጀመር ። ደካሞች እግሩን ይስሙ ዘንድ ፣ እጁን ይነኩ ዘንድ ፣ በእሱም በኩል ይድኑ ዘንድ አመኑ ። ብላቴናው እንደተነገረው ያደርግ ጀመር ።

እነሆ የሚሆን ከመሆን አይቀርምና ቃሉና ቀኑ ደረሰ። ቅንጅት የሚሉት የወያኔ ጠላት ተፈጠረ ። አሕዛብም ለወያኔ ያለውን ተቃውሞ በታላቅ ሰልፍ አሳዬ ።ምርጫም ተካሄደ ። ወያኔ ሕዝብ እንደማይፈልገው ታወቀ ። መከራና ሰቆቃ በወያኔ መንግሥት ውስጥ ደረሰ ። ለቅሶና ሃዘን ምሬትም ወያኔን ወደ ማሠርና ፣ግድያ መራው ። ወያኔ ተከታዮቹን ለክፉ ቀን ያስቀመጣቸውን ፍለጋ ጀመረ ።ቃሉ ይጠበቅ ዘንድ የወያኔ መልክተኛ ለልደቱ እንደገና ታየው ። እንዲህም አለው ፡ -

"እነሆ ጠላቶቼ አሕዛብን ሰብስበው ተነሱብኝ ። ሊያጠፉኝም ጥረት እያደረጉ ነው ። ቃል የገባኸውን ትፈፀም ዘንድ ወደ አንተ መጣሁ።"

ብላቴናውም "ጌታዬ ፈጣሪዬ አሁንም ቃሌን እንደጠበቅሁ ነው።እዘዘኝና የምትፈልገውን ላድርግ ።"

ወያኔም ተደሰተ ።እንዲህም አለው ፡ -

"ድሮም በአንተ እምነት አለኝ ። ቅንጅትን ከፋፍል ። በውስጡ ሽብር ፍጠር ። እንዳይስማሙ አድርግ ። አቋምህ ግልጽ አድርገህ ስለ ሰላምና መረጋጋት አውራ ።እኔም ቅንጅቶችን አስራቸዋለሁ ። አንተን መልሼ ከፍ አደርግሃለሁ ። እንደተቃዋሚም ትወሰዳለህ ። በሬዲዮና በቴሌቪዥን ስምህ እንደገና ይወደሳል ። የተከበሩ አቶ ልደቱም ትባላለህ። የወር ደሞዝህ ይጨመራል ።ጠንክረህ ከፋፍላቸው። የአንተ ክብር በቅንጅት ከርሰ መቃብር ላይ ይመሠረት ዘንድ ተጽፎልና ።"

ብላቴናውም ደስ ብሎት መከፋፈሉን ጀመረ።ድምጹን ከፍ አድርጎ ይሳደብም ጀመር።በአደባባይ የወያኔ ክብር ይሰብክ ጀመር ። አሕዛብም ታላቅ ሃዘን አዘኑ።"**ማንዴላ**" የሚለው ስም **ከህደቱ** በሚለው ተተካ ።

የወያኔ መልዕክተኛም የቅንጅትን ምልክት አካፍሎ ሰጠው ። የተከበሩም አቶ ልደቱ አስባለው ። ከአንባሳደሮች ጋር የኮክቴል ግብዣ ላይ አብሮ እንዲቆም ፈቀደለት ። ሌሎች የሱን ምሳሌነት ይከተሉ ዘንድ ተነገረ ። ብላቴናው 2010 ምርጫ ጥቅሙ አለቀ ። ወያኔም አሽቀንጥሮ ጣለው። በድብቅ ግን የተሰጠውን ድርጎ እየበላ ሆዱ ስለሞላ በደስታ ይኖር ጀመር ።

**እውነት እውነት እላችኋለሁ ለጊዜያዊ ደስታ ሲሉ ሕዝብን የሚክዱ ዘላለማዊ የሆነ የሕዝብ ፍራቻ በሚፈጥረው ጭንቀትና እንቅልፍ ማጣት ያድርባቸው ዘንድ ተፅፏልና በዚህ ጊዜ ተጠንቀቁ ።**

<u>ገድለ ሰለሞን ተካልኝ ( ከዳልኝ )</u>

ብላቴናው የሰፈር ሥርግ ከማድመቅ በላይ ታዋቂነት አልነበረውም ። ዘመኑ በአሕዛብ ላይ ችግር የገባበት ወቅት ስለነበር ሥርግ በመጥፋቱ ከፍተኛ የሆነ ችግር ውስጥ ነበር ። ገንዘብ ወዳድ ስለነበር በችግሩ ምክንያት አምርሮ ያለቅስ ነበር ። ይህንን የሚያውቅ የወያኔ መልክተኛ በግልጽ ታየውና እንዲህ አለው ፡ -

"ተነስና የፖለቲካ ዘፋኝ ሁን
ድድ እንደሌለው አንበሳ ሁሉም በእኔ ላይ ተነሳ
ክብሬም ሞገሴም ተረሳ
ብለህ አቅራራ።ሁሉም ዜሮ ዜሮ ብለህ ጩህ ።እኔ አላስርህምና አትፍራ ። " ትምክተኞች " እንዲከቡህ አደርጋለሁ ። በአሕዛቡ መካከል የተሠገሡጉት ደጋፊዎቼ አንተን ከፍ ከፍ ያደርጉኻል ። ወደ ውጭ አገርም ያወጡሃል ። ቀንህ ደርሶ እስከምጠራህ ድረስ በኢትዮጰያ አንድነት የምታምን ሁን ።" ብሎ አዘዘው።

ብላቴናውም በደስታ መለሰ ፡ -

"ከዚህ መከራ ካወጣኸኝና የንዋይ ፍቅሬን ካቃለልክ ፣ እንደ ጥላሁን ገሠሠ ታዋቂ ካደረከኝ ፣ እነሆ  ቃሌን እስጥሃለሁ ። በፈለከኝ ጊዜ ውለታዬን ልመልስ በታላቁ ስልጣን ሥር ሆኜ ቃል እገባለሁ ። እኔ ምስኪኑ ልጅህ አንተንስ ከጄ የት ልደርስ ። ብሎ ምርር ብሎ አለቀሰ "

ሰለሞን ተካልኝ ታዋቂ ዘፋኝ ሆነ ። ውስጠ ምስጢሩ ያልገባቸው ወደ ላይ አነሱት ። የእውነት ምስክር እንደሆነም ተነገረለት ።አፍቃሪ ነዋይ በመሆኑም ገንዘብ ይፈስለት ጀመር ።

የወያኔ መልዕክተኛ ግን ቀኑን ጠብቆ ብቅ አለ ። እንዲህም አለው ፡ -

በሰሜን በኩል ጠላቶቼ " ትምክህተኞቹን" ሊሰበስቡብኝ ነው ። ለሥልጣኔና ለወንበሬ ያሰጋኛል ። እነሆ ከሥርግ ዘፋኝነት አንስቼ እዚህ እንዳደረስኩህ አትዘነጋም ። ወደ ሰሜንም እሄዳለሁ ብለህ አውጅ ። በሰሜን ካለው ንጉስም ተገናኝ ። እጁንም ሳም ። ሁኔታውን አጥናና በመሣሪያ ሊዋጉኝ በዛ በኩል የሄዱ አሉና በውስጥ ከፋፍላቸው ። ከተመለስክ በኋላ "ሰላማዊ ትግል" ብቻ ነው የሚቻለው ብለህ ተስፋቸውን አስቆርጣቸው ። ወደ ሃገሬ ልመለስ ነው ብለህ አውጅ ። ከዛ አንተንም የሚያበለጽግ እኔንም ሥልጣን ላይ የሚስከርመውን አብረን እናደርጋል ። ልጄ የወገቤ ክፋይ እምነቴ ፣ ተስፋዬ በአንተ ላይ ነው ። ሂድ አሕዛብን አወናብድ ። አለው ። "

ሰለሞን ተካልኝ ሸራተን ሆቴል ዘፍኖ የገንዘብ ክምር ታየው ። ነገ ሃገሬ ልገባ ነው ብሎ አወጀ ። አሕዛብ ተደነቁ ። "ሰለሞን ከዳልኝ" ይሉትም ጀመር ። በትንቢት ተጽፏልና ሰለሞን የተናቀና የተጠላ ሰው ሆነ ። በአሕዛብ ምድር በተፈጠረው ጥላቻ መኖር ስላልቻለ ወደ ሰሜን አሜሪካ ተመልሶ ተሰደደ ። ከውድቀቱ ብዛት ትንሽ የሰሜን ክፍለ ሃገር ሰዎች በሰሜን አሜሪካ በልዩ ልዩ ከተማዎች ሰብስቦ  ሰልፍ በማድረግ ፈጣሪውን ያመስግን ገባ ።

**እውነት እውነት እላችኋለሁ ለጊዜያዊ ደስታ ሲሉ ሕዝብን የሚክዱ ዘላለማዊ የሆነ የሕዝብ ፍራቻ በሚፈጥረው ጭንቀትና እንቅልፍ ማጣት ያድርባቸው ዘንድ ተፅፎልና በዚህ ጊዜ ተጠንቀቁ።**

አሕዛብ የሚቀጥለውን አድርባይ ገድል እየጠበቁ ናቸው ። እነሆ ኃይሌ ገብረ ሥላሴም ይዳዳዋል ፣ ብዙዎቹም መፃፍ ጀምረዋል ። ታሪካቸው ይመዘገባል ። የተዋረዱ ናቸውና እንዳፈሩ ይኖሩ ዘንድ በሕዝብ ተፈርዶባቸዋል ። ከዚህ ዓይነት የሰቀቃ ኑሮ ያውጣን ።

*ተፈፀመ*
ይቀጥል ይሆን ። ገድለ አድርባይ እስካለ ድረስ አይቆምም ።

ስለሕዝብ ብለው መሰዋዕትነት የሚከፍሉ በሰላም ይክረሙ !
ፍራንክፈርት ጥቅምት 2010
<u>beljig.ali@gmail.com</u>